AABE
Accounting and Auditing Board of Ethiopia
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ

ከኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ኢኮኖሚ

# የፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ሚና ለአጀንዳ 2063

የፓን አፍሪካ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን (PAFA) ለአጀንዳ 2063 ውጤታማነት ያለው ሚና ጉልህ ነው። ይህም በቀጣዮቹ አራት አስርት ዓመታት ለአፍሪካ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንደ አንድ ስትራቴጂካዊ ማዕቀፍ የሚቆጠር ነው። ፌዴሬሽኑ በአፍሪካ የሂሳብ ሙያን የሚወክል እና በአህጉሪቱ ከፍተኛ የአካውንታንሲ እና የፋይናንስ አስተዳደር ደረጃዎችን የሚያስተዋውቅ የሙያ ድርጅት ነው። በአጠቃላይ ፌዴሬሽኑ ከዓለም ዓቀፉ አካውንታንቶች ፌዴሬሽን (IFAC) ጋር በመቀናጀት የአካውንታንሲ ሙያው እንዲጠናከር፣ የፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን፣ የሕዝብ/ የመንግሥት የፋይናንስ ዘርፍ አስተዳደር እንዲሻሻል፣ ተያያዥ ፖሊሲዎች በተገቢው እንዲፈፀሙ እና በአፍሪካ ለዘላቂ ልማት ያላሰለሰ አስተዋጽኦ በማድረግ የአጀንዳ 2063ን ውጤታማነት በመደገፍ ወሳኝ ሚና ሊጫወት የሚችል አፍሪካዊ ተቋም ነው።

አጀንዳ 2063ን ስንመለከት በጥቅሉ አፍሪካን ወደ መጪው የዓለም ኃይል ለመለወጥ የተዘጋጀ ንድፍ እና ማስተር ፕላን ነው የሚል መልስ እናገኛለን። የአንድነት፣ የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ የነፃነትን፣ የእድገት እና የጋራ ብልፅግናን የሚያንፀባርቀው የፓን አፍሪካኒዝም እና የአፍሪካ ሕዳሴ ተጨባጭ መገለጫ የሆነው ይህ አጀንዳ፤ ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ ልማት ለማሳካት ያለመ ተስፋ የሚጣልበት የአህጉሪቱ ስትራቴጂካዊ ማዕቀፍ ነው።

ታዲያ የዚህ አጀንዳ የመፈጠሩ ዋነኛው ምክንያት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ትኩረት ለነበረው ለአህጉሪቱ የቅኝ ግዛት ሰለባ የፖለቲካ ነፃነት ለማስገኘት እንዲሁም፤ አፓርታይድን ከመታገል አንፃር የአፍሪካን አጀንዳ እንደገና ማጤን እና መገምገም ነበረበት የሚለውን ሃሳብ የአፍሪካ መሪዎች ቆይተውም ቢሆን በ1963 መገንዘባቸው ነው። ይሄውም የአፍሪካ ሕብረት ቀዳሚ ተግባር ሁሉን አቀፍ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ አህጉራዊና ክልላዊ ውህደት፣ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲሁም ከሌሎች ሕዝቦች ጋርም ቢሆን ሰላምና ደህንነት በመፍጠር አፍሪካን በዓለም አቀፍ መድረክ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንድትሆን ማድረግ ነው።

ይህንን ሁሉን አቀፍ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትና ልማትን ማስገኘት ለሚያስችለው መንገድ ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሳየት እ.ኤ.አ በግንቦት ወር 2013 የአፍሪካ ሕብረትን 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ የአፍሪካ መንግሥታት እና መሪዎች የስምምነት መግለጫ ተፈራረሙ። መግለጫው የተቀናጀ፣ የበለፀገችና ሰላማዊ፣ በራሷ ዜጎች የምትመራ፣ በዓለም አቀፍ መድረክ ውስጥ ተለዋዋጭ ኃይልን የምትወክል አፍሪካ የሚለውን የፓን አፍሪካ ራዕይ ለማሳካት አፍሪካ እንደገና መነሳቷን በደንብ ያስረግጣል። ለዚህም አጀንዳው አህጉሪቱ ይህንን ራዕይ እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2063 ባለው የ50 ዓመት የጊዜ ርዝማኔ ውስጥ ለማሳካት ያሰበችበት ተጨባጭ መግለጫ ነው።

አጀንዳ 2063 'የምንፈልጋት አፍሪካ' በሚል መሪ ሀሳብ አህጉሪቱ ለ50 ዓመት የምትመራበትን እቅድ የያዘ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ ሰባት ዓላማዎችና ዋንኛ የትኩረት አቅጣጫዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ሁሉን አቀፍ በሆነ እድገትና ዘላቂ ልማት የበለጸገች አፍሪካን መፍጠር፤ በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤዎችና በአፍሪካ ሕዳሴ ራዕይ አማካኝነት የተሳሰረና ፖለቲካዊ አንድነት ያለው አህጉር እውን ማድረግ፤ አፍሪካን መልካም አስተዳደር የሰፈነበት፣ የሰብአዊ መብቶችና የሕግ የበላይነት የሚከበርበት፣ ፍትሕ የነገሰበትና ዴሞክራሲያዊ አህጉር ማድረግ፤ ሰላሙንና አንድነቱን የጠበቀ አፍሪካን መፍጠር፤ ጠንካራ የባህል ማንነት፣ የጋራ ቅርስና እሴቶች ያሉት እንዲሁም ጠንካራ ማኅበረሰባዊ የሞራል መሰረት የፈጠረ አፍሪካን ማየት፤ የአፍሪካ ልማት ዜጎችን ማዕከል ያደረገ፣ የአፍሪካን ሕዝብ በተለይም የወጣቶችና ሴቶችን አቅም የሚጠቀምና ለሕጻናት ክብካቤ ትኩረትን የሰጠ እንዲሆን ማድረግ እና ጠንካራ፣ አንድነቱን የጠበቀ፣



ከፊል የመድረኩ ተሳታፊዎች

የማይበገርና በዓለም መድረክ ተጽእኖ ፈጣሪና አጋር የሆነ አፍሪካን መፍጠር የሚሉት ናቸው።

እነዚህን ምኞቶች ለማሳካት የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የሰው ኃይል ልማት እና አቅም ግንባታ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ፣ የኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ የግብርና እና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የፆታ እኩልነት፣ ሰላምና ደህንነት እና የአካባቢያዊ ደህንነት ዘላቂነት የመሳሰሉት አፅንኦት የሚሹ ዋና ዋና መስኮች ሲሆኑ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ቀጣናዊ ውህደትና ትብብር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው።

ታዲያ ይህንን አጀንዳ 2063 በተግባር ተገልጦ ውጤታማ እንዲሆን እና በአጀንዳው በ50 ዓመት ውስጥ ልናያት ያለምናትን አፍሪካን ለማየት በሁሉም ዘርፍ ወጥነት ያለውና በሁሉም ሀገራት የሚተገበር የአሰራር ስርዓት ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ እጅጉን አስፈላጊ ነው።

በፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (PAFA) ከመጋቢት 10 እስከ 13 2016 ዓ.ም ለተከታታይ አራት ቀናት በአዲስ አበባ ከተማ የተዘጋጀው መድረክ በአጀንዳ 2063 አፍሪካን በተለያዩ ዘርፎች አንድ ለማድረግ የታቀደውን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚረዱ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው። የመድረኩ ዓላማም በአህጉር ደረጃ ወጥ የሆነ የኦዲት ሪፖርት እንዲኖር የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ጥራት ያለው፣ ተዓማኒ እና በመላው ዓለም ተቀባይነት ያለው የኦዲት ሪፖርት እና ባለሙያ ማፍራት የሚያስችል ሁሉም አፍሪካውያን የሚጠቀሙበት የአሠራር ማንዋል ለማጽደቅ ነው። በዚህ መድረክ ከ22 ሀገራት የተውጣጡ 38 የሂሳብ ባለሙያዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በአፍሪካ የሂሳብ ሙያን ለማሳደግ በምናደርገው ጥረት ትብብር ቁልፍ ሚና እንዳለው የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ኢዮብ ተካልኝ በመክፈቻ ንግግራቸው አስታውሰዋል። በፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን እና በቦርዱ መካከል ያለው ትብብር ተግዳሮቶችን ለመፍታት እና በፊታችን ያሉትን እድሎች ለመጠቀም የሚያስፈልገውን የትብብር መንፈስ እና የጋራ ተግባርን ያሳያልም ብለዋል። በጋራ፣ የጋራ እውቀታችንን እና ሀብታችንን ተጠቅመን አወንታዊ ለውጥ ለማምጣት እና ለአህጉራችን ኢኮኖሚያዊ ልማት እና ብልጽግና ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ ለማበርከት ትብብር ቅድሚያ የምንሰጠው ተግባር ነው ብለዋል ዶክተር ኢዮብ።

በተመሳሳይም በመድረኩ የተጋበዙት የፌዴራል ዋና ኦዲተር እና የቦርዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ እንደተናገሩት፤ በመንግሥት ተቋማት የዓለም ዓቀፍ የፐብሊክ ሴክተር አካውንቲንግ ስታንዳርድን ተግባራዊ ለማድረግ ኢትዮጵያ በጅምር ላይ መሆኗን ጠቅሰው ቀድመው ስታንዳርዱን ከተገበሩ የፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን አባል ሀገራት ተሞክሮ ለመውሰድ ምቹ አጋጣሚ መሆኑን ተናግረዋል።

ፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (PAFA) በአፍሪካ ውስጥ የሂሳብ ሙያ በሚመለከት የሚሠራ ድርጅት ነው። ድርጅቱ በ45 ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ 56 አባል ድርጅቶችን እና አምስት ዓለም አቀፍ ተባባሪዎችን ያካተተ ነው። የአፍሪካን ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ዘላቂ እሴት መፍጠርን ራዕዩ አድርጎ የሚሠራ ሲሆን በአፍሪካ ውስጥ ያለውን የሒሳብ ሥራ አቅም እና ተፅእኖን ለማጠናከር የንግድ ልውውጥን፣ የአገልግሎት ጥራትን እና በተቋማት ላይ እምነት መጣልን ተልዕኮው አድርጎ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው።

ፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (PAFA) የሂሳብ ሙያን ለመቆጣጠር በመላው አፍሪካ የተተገበሩ ሞዴሎችን ልዩነት ያውቃል። ስለዚህ ዓላማው አንድን ሞዴል ማስተዋወቅ ሳይሆን ውጤታማ፤ ሀገር-ተኮር፤ ለዓላማ ተስማሚ ሞዴል መሥራት ነው። የእንቅስቃሴው ዓላማ በአፍሪካ ውስጥ በሀገር ደረጃ የሚተገበር አህጉራዊ መፍትሄ በማምጣት የጥራት ማረጋገጫ ግምገማ ሥርዓቶችን ማስማማት ነው።

ከፍተኛ ጥራት ያለው የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና ኦዲት መካተት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን በመቀበል፣ ደረጃዎቹን በመደገፍ ደረጃውን የጠበቀ ትግበራን መደገፍ እና በሂሳብ አያያዝ ሙያ የአተገባበሩን ጥራት መከታተል ለማንኛውም የንግድ ሥራ ስኬት ወሳኝ ነው።

በመድረኩ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የPAFA የሂሳብ ጥራት አማካሪ ቡድን ሊቀመንበር ጆርጅ ማኩዋ፤ የሒሳብ አያያዝ ጥራት ለኢኮኖሚያችን ጤና እና ለካፒታል ገበያችን ስኬታማ ሥራ ያለውን መሠረታዊ ጠቀሜታ ገና ከጅምሩ ማጉላት አስፈላጊ ነው። ይህ በጣም በቅርብ ጊዜ ታይቷል፤ ዋና ዋና ኩባንያዎች ባልተጠበቀ ሁኔታ ሲወድቁ እና ውጤቶቹ ለባለሀብቶች፣ ለሠራተኞች፣ ለአቅራቢዎች፣ ለጡረተኞች፣ ለደንበኞች እና ለመንግስት ከፍተኛ ኪሳራ ሊሆኑ ችለዋል፣ በቀጣይም ስጋት ሊሆኑ ይችላሉ።

ቀጣይነት ባለው ስራው፣ የPAFA የሂሳብ አያያዝ ጥራት አማካሪ ቡድን በአፍሪካ ውስጥ የባለሙያ የሂሳብ አያያዝ አገልግሎቶችን ጥራት እና ተንቀሳቃሽነት ለማሳደግ የPAFA ስትራቴጂካዊ ዓላማን ለማሳካት አስተዋፅዖ ያደርጋል። ከኦዲት ጥራት እና የኦዲት ደረጃዎች ጋር በተገናኘ የጋራ ግንዛቤን እና የጋራ ምላሾችን ማዳበር፤ የPAFA የጥራት እና የእንቅስቃሴ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ ማዕከል ነው። አባላት የተቀናጁ አቀራረቦችን/ integrated approaches/ የሚገነቡበት እና ምርጥ ተሞክሮዎችን የሚያራምዱበት መሰረት ይጥላል።

በአፍሪካ ያለውን የኢኮኖሚ ትስስር (በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት (AfCFTA) እና የኦዲት ኔትወርኮች እና ከደንበኞቻቸው ዓለም አቀፋዊ አሠራር በመነሳት ከፍተኛ ጥራት ያለው ኦዲት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስፈልጋል። ልናሳካው የምንፈልገው ተፅዕኖ በንግድ ላይ እምነት እንዲጨምር፣ በመንግሥት ላይ እምነት እንዲጨምር፣ የውጭ ቀጥታና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እና የልማት ፋይናንስን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያግዝ ከፍተኛ ጥራት ያለው የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረብ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሂክመት አብደላ እንደተናገሩት፤ ፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (PAFA) መቀመጫውን በደቡብ አፍሪካ ያደረገ ተቋም ሲሆን የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድም በዚህ ተቋም ውስጥ አባል ከሆነ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል።

ቦርዱ ከጥራት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። የጥራት ችግር ከበፊትም የነበረ ነው። አሁን ላይ ኦዲተሮቻችንን ለማብቃት በርካታ ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን። ከቁጥጥር በፊት ባለሙያውን ማብቃት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ማብቃት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራበት ቆይቷል። የጥራት ቁጥጥር ሥራ ከተጀመረ ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል።

የአፍሪካ አህጉራዊ የነፃ ገበያ ስምምነት፤ የባለሙያዎችን በነፃነት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚደግፍ ሃሳብ በውስጡ ያካተተ ነው። ይህም በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ያሉ ኦዲተሮች ከሀገራቸው ውጪ ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ተዘዋውረው መሥራት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎች ተመሳሳይ ሙያዊ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል። በፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን (PAFA) ደረጃ ማኑዋል እንዲዘጋጅ የተደረገውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ለአራት ቀን የተካሄደው ይህ መድረክ ወጥነት ባለው መልኩ የኦዲት ቁጥጥር ሲደረግ በምን አይነት ሥርዓት መሆን አለበት የሚለውን ሃሳብ ያካተተ ነው። በአፍሪካ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለው የኦዲት ቁጥጥር ሥርዓት በሁሉም ሀገራት ተግባራዊ እንዲደረግ በፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን መሠራት ከተጀመረ አንድ ዓመት ሆኖታል።

አሁን ባለው አሠራር የሂሳብ ሥራን ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው ሀገር እየተዘዋወሩ ለመሥራት የሚቻል አይደለም። የአፍሪካ አህጉራዊ የነፃ ገበያ ስምምነትም፤ የባለሙያዎችን በነፃነት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚደግፍ ሃሳብ የያዘ ቢሆንም አሁን ባለንበት ደረጃ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ያስቸግራል። ነገር ግን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት አሁን ላይ ሥራዎች በመሠራት ላይ ይገኛሉ። የፓን አፍሪካ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ዓላማም ይሄው ነው።